የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

## OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፫
አዲስ አበባ — ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

7[th] Year No. 3
ADDIS ABABA - 30[th] November, 2000

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፩/፲፱፻፺፫ ዓ.ም
የኢትዮ—ሱዳን የንግድ ስምምነት ማጽደቂያ
አዋጅ ........................................... ገጽ ፩ሺ፬፻፳፱

CONTENTS

Proclamation No. 221/2000
Ethio-Sudan Trade Agreement Ratification
Proclamation ........................................ Page 1429

## አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፩/፲፱፻፺፫
## ከሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት ጋር የተደረገውን የንግድ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል የተደረገው የንግድ ስምምነት እ.ኤ.አ. ማርች ፮ ቀን ፪ሺ.ህ በካርቱም የተፈረመ ስለሆነ፣

ስምምነቱ በሥራ ላይ የሚውለው ተዋዋዮቹ ሀገሮች በየሕገ መንግሥታዊ ሥርዓቶቻቸው መሠረት ስምምነቱ መጽደቁን አንዱ ለሌላው ካሳወቀበት የመጨረሻው ቀን ጀምሮ እንደሚሆን በስምምነቱ ውስጥ የተገለጸ በመሆኑ፣

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያጸደቀው በመሆኑ፣

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

፩· <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ “ የኢትዮ—ሱዳን የንግድ ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፪፻፳፩/፲፱፻፺፫” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪· <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በሱዳን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል እ.ኤ.አ ማርች ፮ ቀን ፪ሺ.ህ በካርቱም የተፈረመው የንግድ ስምምነት ጸድቋል።

## *PROCLAMATION NO. 221/2000*
## *A PROCLAMATION TO RATIFY THE TRADE AGREEMENT WITH THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF THE SUDAN*

WHEREAS, an Agreement, on Trade, between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of the Sudan was signed in Khartoum, Sudan, on the 6[th] day of March, 2000;

WHEREAS, it is stipulated in the Agreement that the Agreement shall enter into force after the later date on which the Governments of the contracting parties have notified each other that their constitutional requirements for the entry into force of the Agreement have been fulfilled;

WHEREAS, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 30[th] day of November, 2000;

NOW, THEREFORE, in accordance with Sub-Articles (1) and (12) of Article 55 of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the ''Ethio-Sudan Trade Agreement Ratification Proclamation No. 221/2000''.

2. *Ratification of the Agreement*

   The Ethio-Sudan Agreement on Trade signed in Khartoum on the 6[th] day of March, 2000 is ratified.

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፫· የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ሥልጣን
የንግድና ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር ስምምነቱ በሥራ ላይ እንዲውል ለማድረግ በዚህ አዋጅ ሥልጣን ተሰጥቶታል።

፬· አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ
ይህ አዋጅ ከኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፫ ዓ·ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

3. *Power of the Ministry of Trade and Industry*
The Ministry of Trade and Industry is hereby empowered to implement the Agreement.

4. *Effective Date*
This Proclamation shall enter into force as of the 30th day of November, 2000.

Done at Addis Ababa, this 30th day of November, 2000.

NEGASO GIDADA (DR.)
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE